# የኤፌሶን ጥናት #2 (37)

## ጥናት አንድ ኤፌ 1፡1-14

የጥናት ዓላማ፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን ደህንነትን የተቀበልን ሁላችን፣ ወደፊት እንድንወርስ እግዚአብሄር ላዘጋጀልን ርስት መያዣና ዋስትና እንዲሆን መንፈስ ቅዱስን በውስጣችን ስላኖረ ልናመሰግነው እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…የእውነትን ቃል ይህም የድነታችሁን ወንጌል በሰማችሁ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ተጨምራችኋል፤ አምናችሁም በእርሱ በመሆን ተስፋ ሆኖ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ታትማችኋል፡፡›› ኤፌ 1፡13

1. ኤፌ 1፡1-14 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ላይ ስትመለከት የኤፌሶንን መልዕክት የተጻፈው በማን ነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ መልዕክቱ ስለተጻፈላቸው ሰዎች የተነገረላቸው ቢንስ አራት እውነቶችን ዘርዝር፡፡ የጸጋና የሰላም ምንጭ ሆኖ በዚህ ክፍል የሚነገርለት ማን ነው?
2. በቁ3 ላይ ጳውሎስ ስለምንድነው እግዚአብሄርን ሲባርክ የምናየው? ስለዚህ ስለተባረክነው የበረከት ዓይነትና ሁኔታ ከዚህ ክፍል መረዳት የምንችላቸው ቢያንስ አምስት ለመዘርዘር ሞክር፡፡ እግዚአብሄር ይህንን ሁሉ በረከት በተለይም ከእርሱ ጋራ የመታረቅን በረከት ስለሰጠህ ምን ያህል ትባርከዋለህ?
3. በ4-6 መሰረት የተመረጥንበት ዓላማ ምንድነው? እኛ የተመረጥነው ጥሩ ጸባይ ስላሳየን፣ ቁንጆዎች ስለሆንን፣ ከሃብታም ቤተሰብ ስለመጣን ወይም ከንጹህ ዘር ስለተወለድን አለመሆኑን ከነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ግልጽ አድርጎ የሚነግረን ሃሳብ የትኛው ነው? ምርጫው በማን በኩል እንደመጣ ነው ክፍሉ የሚነግረን?
4. ሌላው በቁ4-6 ውስጥ በክርስቶስ በኩል የተደረገልን ትልቅ ነገር ምንድነው? እነዚህን ቁጥሮች ስታነብ፤ እግዚአብሄር አብ ይህንን ሁሉ በጎና መልካም ነገር ሁሉ ለማድረግ የገፋፋው ነገር ምንድነው ብለህ ትገምታለህ?
5. በቁ7-9 ላይ እግዚአብሄር እንዳደረገልን የሚናገራቸው ተጨማሪ ነገሮች ምን ምንድናቸው? ‹‹የሃጥያትን ይቅርታ አገኘን›› የሃጥያትን ይቅርታ ማግኘት የቻልንበት መንገድ እንዴት እንደሆነ አስረዳ? ሃጥያትህ ይቅር እንደተባለልህ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛነት ይሰማሃል ወይ?
6. ቁ10-12ትን ስናነብ የወደፊት ዕቅድ የሚነግረን ነገር ምንድነው? ቁ3፣ ቁ4፣ ቁ5፣ ቁ6፣ ቁ7፣ ቁ9፣ ቁ12ትን ስንመለከት ‹‹በክርስቶስ›› ወይም ‹‹በእርሱ›› ወይም ‹‹በኢየሱስ›› የሚሉትን አነጋገሮች እናነባለን፡፡ ለምን ይመስልሃል ይህ የክርስቶስ ስም ይህንን ያህል ትልቅ ስፍራ የተሰጠው?
7. በቁ13-14 ላይ ስናነብ ወደ ክርስቶስ ለመጨመርና የክርስቶስ ወገን ለመባል ቅድመ ሁኔታ ሆኖ የተነገረው ነገር ምንድነው? ቁ13 ላይ በፍጹም ልቡ በክርስቶስ ላመነ ሰው በተጨማሪ ከእግዚአብሄር ዘንድ የሚደረግለት ምን ትልቅ ነገር ታያለህ?
8. ቁ14 ላይ ስለታተምንበት መንፈስ ቅዱስ ሲናገር ‹‹እርሱ ለርስታችን ዋስትና የሚሆን መያዣ ነው፡፡›› ሲል ምን ትረዳለህ? በክርስቶስ ባመንክ ዕለት እግዚአብሄር በሰማይ ስላዘጋጀልህ ርስት ዋስትና የሚሆን መያዣ በውስጥህ መንፈሱን እንዳኖረ ተረድተሃል ወይ? መኪናም ሆነ ቤት ስንገዛ ቀሪውን ሂሳብ እንደምንከፍል ለማረጋገጥ ቀብድ እንደምንከፍል ሁሉ እግዚአብሄርም ወደፊት ርስተን እንዳዘጋጀልን የገባልንን ቃል ኪዳን እንደሚፈጽም መያዣና ዋስትና አድርጎ መንፈሱን በውስጣችን አኑሯል ቁ14 ይነበብ፡፡

# ጥናት ሁለት ኤፌ 1፡15-23

የጥናት ዓላማ፡- በቤተ ክርስትያን ውስጥ በበላይነት እንዲመሩን እግዚአብሄር የሚያስቀምጣቸው ሰዎች እንዳሉ ብናውቅም፤ የሁሉ የበላይና አዛዥ የሆነው ኢየሱስ አካሉ ለሆነችው ለቤተክርስትያን ራስ ስለሆነ እያንዳንዳችን ለእርሱ የመገዛትና የመታዘዝ ሃላፊነት እንዳለብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በቤተ ክርስትያንም በማንኛውም ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾመው፡፡ እርሷም ሁሉን ነገር በሁሉም ረገድ የሚሞላው የእርሱ ሙላት የሆነች አካሉ ናት፡፡›› ኤፌ 1፡22-23

1. ኤፌ 1፡15-23 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ15-16ትን ስናነብ በኤፌሶን በሚገኙት ቅዱሳን ህይወት ውስጥ ተገልጠው የሚታዩት ሁለት መልካም ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ ስለ እነዚህ ሰዎች ሲያደርግ የምናየው ነገር ምንድነው? በአንተስ ከራስህ አልፈህ በእግዚአብሄር ፊት የምትጸልይላቸውና የምታመሰግንላቸው ሰዎች በህይወትህ ውስጥ አሉህ ወይ?
2. በቁ15 ላይ በኤፌሶን ሰዎች የምናያቸው ሁለት ነገሮች፤ ማለትም በኢየሱስ ማመንና ቅዱሳንን ማፍቀር በክርስትና ህይወት ውስጥ አስፈላጊነታቸውንና አንደኛው ከሌላው ጋራ ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ምን ሊሆን እንደሚገባ አስረዳ፡፡
3. በዛሬው ምንባብ ውስጥ ሐዋርያው የሚጸልይላቸው ሰዎቹ የሌላቸው ነገር እንዲሰጣቸው ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? አይደለም ካልክ ታዲያ ጸሎት መጸለይ ለምን አስፈለገው?
4. 1ኛ ቆሮ 2፡12 ላይ ‹‹ከእግዚአብሄር የሆነውን መንፈስ እንጂ የአለምን መንፈስ አልተቀበልንምና፣ ይህም እግዚአብሄር በነጻ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ ነው፡፡›› ኤፌ 1፡17 ደግሞ ‹‹የጥበብና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ ያለማቋረጥ እለምናለሁ›› ይላል፡፡ ከነዚህ ጥቅሶች አንጻር ጳውሎስ የጥበብና የመገለጥን መንፈስ መለመን ቅድሚያ የሰጠበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ?
5. ቁ18-19ን በማንበብ ስለ ‹‹ተስፋ›› ስለ ‹‹ርስት››፣ እና ስለ ‹ሃይል›› ሲጸልይላቸው እናያለን፡፡ የኤፌሶን ሰዎች እነዚህን ሶስት ነገሮች መረዳትና ማወቅ እንዲችሉ ጳውሎስ የሚጸልየው ጸሎት ምንድነው ምንድነው? ሰዎች መንፈሳዊ እውነትን ለመረዳት ሲቸገሩ ስናይ እኛ ማድረግ ስለሚገባን ነገር ወይም ደግሞ እንደ እኛ መጽሐፍ ቅዱስን ለሚያጠኑ ሰዎች ይህ ክፍል ምን ያስተምራል ብለህ ታምናለህ?
6. ቁ19-21 በተለይም በቁ19 ላይ ‹‹ለእኛ ለምናምነውም ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን ሃይሉን እንድታውቁ…›› በማለት የሚናገረውን ሃይል በቁ20 አነጋገር መቼ ነው ግልጽ ሆኖ የታየው? ለምን ይመስልሃል ክርስቶስን ከሞት ለማስነሳት ትልቅ የሆነ ሃይል የሚያስፈልገው?
7. በቁ21-22 ላይ በማንበብ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት የሚያሳዩንን ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር፡፡
8. ቁ22 ላይ ‹‹በቤተ ክርስትያንም…ራስ አድርጎ ሾመው፡፡›› ይላል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስትያን ራስ ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ነው የምትረዳው? አካላችን ሁሉ ከራስ ትዕዛዝን እንደሚቀበል አንተስ ጌታ በቃሉ የሚያዝህንና የሚነግርህን ለመታዘዝ ምን ያህል ትተጋለህ? ኢየሱስ አካሉ ለሆነችው ለቤተ ክርስትያን ራስ አድርጎ ስለሰጠው ሁላችን ልንታዘዘውና ያለንን ልንታዘዝ የሚገባን ለኢየሱስ እንደሆነ ልናውቅ ይገባናል፡፡

# ጥናት ሶስት ኤፌ 2፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- ደህንነት የሰው አስተዋጽኦ የሌለበትና እግዚአብሄር ብቻውን ሰርቶ የጨረሰው የጸጋ ስጦታ መሆኑን ተረድተን እንዲሁ በእምነት በመቀበል እርሱን የምናመሰግንበት ነገር እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በእምነት በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሄር ሥጦታ እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም›› ኤፌ 2፡8-9

1. ኤፌ2፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ላይ የምናነበው ነገር ስለማን የተነገረ ነው ብለህ ታምናለህ? ለምን ይህንን ማለት ቻልክ? እነኚህ ቁጥሮች ቀድሞ ስለነበርንባቸው ሁኔታዎች የሚነግሩንን ነገሮች ሁሉ በቅደም ተከተል ዘርዝር፡፡
2. ቁ1 ‹‹ነበራችሁ›› ቁ2 ‹‹ትኖሩ ነበር›› ቁ3 ‹‹እንኖር ነበር›› የሚሉት አነጋገሮች የሚጠቁሙን እውነት ምንድነው? ይህ ክፍል አንድ ሰው በክርስቶስ ውስጥ እስካልሆነ ድረስ በሃጥያቱና በበደሉ ምክንያት ምውት መሆኑን ይነግረናል፡፡ ሰው ቆሞ እየሄደና እየተራመደ እንዴት ነው በእግዚአብሄር ዓይን ምውት ነው ሊባል የሚችለው? አንተስ በእግዚአብሄር ዓይን ስትታይ ምውት ነህ ወይስ ህያው?
3. ብዙ ጊዜ ለክርስትያን ጠላቶች በመባል የሚነገሩት ዓለም፣ ሥጋና፣ ሰይጣን ናቸው፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሶስቱ የአማኝ ጠላቶች የት የት ሥፍራ ተጠቅሰው እንደሚገኙ ተናገር፡፡ ቁ2 ላይ ‹‹…አሁንም ለእግዚአብሄር በማይታዘዙት ሰዎች ላይ ለሚሰራው መንፈስ እየታዘዛችሁ ትኖሩ ነበር›› የሚለው በክርስቶስ ያላመኑ ሰዎች ስለሚኖሩበት ሁኔታ ከዚህ አነጋገር ምን ትረዳለህ?
4. በቁ4 ላይ ‹‹ነገር ግን›› የሚለው አነጋገር ለምንድነው ለእኛ በጣም አስገራሚ ቃል ሆኖ የሚታየው? የእግዚአብሄር ሙታን የነበርነውን እኛን ወደራሱ ለመመለስ የገፋፋትን ቢያንስ ሶስት ባህርያቱን ከቁ4-7 ውስጥ በማውጣት ተናገር፡፡
5. በቁ4-7 ላይ ቀድሞ ሙታን በነበርነው ሰዎች ህይወት ውስጥ ስለመጡት ለውጦች ሰፍረው የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ በዝርዝር ተናገራቸው፡፡ በቁ6 ላይ‹‹…በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋራ አስቀመጠን›› በማለት ይናገራል፡፡ እኛ በምድር ላይ እንዳለን እየታየ፤ ምን ማለቱ ነው በሰማያዊ ሥፍራ ተቀምጠናል በማለት የሚነግረን?
6. ደህንነታችን አስመልክቶ ቁ8-9ኝን ብቻ በመመልከት ልንረዳ የምንችላቸውን ሃሳቦች በሙሉ ሰፋ አድርጋችሁ ተነጋገሩባቸው፡፡ ለምንድነው ‹‹ማንም እንዳይመካ›› በማለት በቁ9 ላይ የሚያስጠነቅቀን?
7. ኤፌ 2፡9 ላይ ያለው ሃሳብና 1ኛ ቆሮ 1፡29-31 የሰፈረው በሥራ መጽደቅንና ትምክህትን አስመልክቶ የሚናገሩት ሃሳብ በምን መንገድ እንደሚደጋገፍ አስረዳ፡፡
8. ቁ9 ላይ የሚናገረው ሥራና በቁ10 ላይ የሚናገረው ሥራ ልዩነታቸው ምን ይመስልሃል? አንተስ የምትሰራው ደህንነትን ከእግዚአብሄር ለመግዛት ነው ወይስ በነጻ ለተቀበልከው ደህንነት የምስጋና መስዋዕት እንዲሆንልህ ነው? ኢሳ 64፡6 ቢነበብ ይረዳል፡፡ ደህንነት የሰው አስተዋጽኦ የሌለበትና እግዚአብሄር ብቻውን ሰርቶ የጨረሰው የጸጋ ስጦታ ስለሆነ በእምነት ተቀብለን እርሱን የምናመሰግንበት ነገር እንደሆነ ልናስብ ይገባናል፡፡

# ጥናት አራት ኤፌ 2፡11-22

የጥናት ዓላማ፡- እኛ ሁላችንም በዘር፣ በጎሳ፣ በሃብት፣ በትምህርትና በሌሎችም ነገሮች የተለያየን ብንሆን፤ ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞቱ ምክንያት ይህ ሁሉ ልዩነት ቀርቶ ሁላችንም የእግዚአብሄር ቤተሰብ ውስጥ በመግባት ወንድምና እህት እንደሆንን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ከዚህ የተነሳ እናንተ ከቅዱሳን ጋራ የአንድ አገር ዜጋ፣ የእግዚአብሄርም ቤተሰብ አባል ናችሁ እንጂ፤ ከእንግዲህ ወዲህ መጻተኞችና እንግዶች አይደላችሁም፡፡›› ኤፌ 2፡19

1. ኤፌ2፡11-22 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ11-12 ላይ በትውልዳቸው አህዛብ የነበሩት አማኞች ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲያስቡና እንዲያስታውሱ የሚነግራቸው ነገር ምንድነው? ለምን ይመስልሃል ቀድሞ የነበሩበትን ሁኔታ ማስታወስ የሚጠቅመው?
2. ቁ11 ‹‹ቀድሞ›› ቁ13 ‹‹አሁን ግን›› ቁ19 ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ›› የሚሉት አነጋገሮች የሚያረጋግጡልን እውነት ምንድነው ብለህ ታምናለህ? በቁ13 አነጋገር አሁን ያሉበት ሁኔታ በምን መንገድ ነው ከቀድሞው ሁኔታቸው የሚለየው?
3. በቁ14-15 ላይ ‹‹ሁለቱን›› በመባል የተነገረላቸው ማንና ማን ናቸው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ክርስቶስ የሰራቸው ሥራዎች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
4. በቁ14-15 ላይ ክርስቶስ ሲያስታርቅ የምናየው ማንን ነው? በቁ16 ላይስ እርቁ የተካሄደውበማንና በማን መካከል ነው? በተለይም አህዛብንና አይሁድን ሲያስታርቅ የክርስቶስ ዓላማው ምን እንደነበረ ነው የምንረዳው?
5. ቁ16ትን ስንመለከት፤ በክርስቶስ መስቀል እንደተከናወኑ የምናያቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ክርስቶስ ጥልን በመስቀሉ ገደለ የሚለው ሃሳብ ዛሬ በህይወታችን ሊያስከትል የሚገባው ለውጥ ምንድነው ብለህ ታምናለህ? ይህ እውነት ምን ያህል በህይወትህ ለውጥ አምጥቷል?
6. 18ትን ከዘፀ 19፡20-24 ጋራ አገናዝበህ በማንበብ በሁለቱ ክፍሎች መካከል የምታየውን ልዩነት አስረዳ፡፡ በእነዚህ ሁለት ክፍሎች መካከል የሚታየው ልዩነት የመጣው በምን ምክንያት ነው? ይህንን በክርስቶስ ደም የተገኘልህን ወደ አብ የመቅረብ መብት ምን ያህል ትጠቀምበታለህ?
7. በቁ19-22 ባለው ክፍል ውስጥ ክርስቶስ አህዛብንና አይሁድን አንድ በማድረግ ስለፈጠረው አዲስ ሰው የተነገሩት ቢያንስ ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
8. በተለይ በቁ19 ላይ ‹‹የእግዚአብሄር ቤተሰብ አባል ናችሁ›› የሚለው አነጋገር ከእግዚአብሄር ጋራ ስላለህ ቅርበት የሚያሳይህ ነገር ምንድነው? ለሌሎች ቅዱሳንስ ሊኖርህ የሚገባህን አመለካከትስ በምን መንገድ ሊቀይረው ይገባል ብለህ ታምናለህ? ምንም እንኳን በዘር፣ በጎሳ፣ በሃብት፣ በትምህርትና በመሳሰለው ነገር ሁሉ የተለያየን ብንሆን፤ የክርስቶስ ሞት ሁላችንንም የእግዚአብሄር ቤተሰቦች ስላደረገን ሁላችንም ወንድማማች ሆነናል፡፡

# ጥናት አምስት ኤፌ 3፡1-21

የጥናት ዓላማ፡- ተሰፍሮ ሊያልቅ የማይችለውን የክርስቶስን ፍቅር ለመረዳትና ለመገንዘብ ከመጣራችን ጋራ፤ እኛም የእርሱ ተከታዮች የሆንን ሁላችን ፍቅራችን እንደዛፍ ሥር ወደታች እንደ ህንጻ ደግሞ ወደላይ የሚያድግ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ደግሞም ሥር ሰዳችሁ፣ በፍቅር ታንጻችሁ፣ የክርስቶስ ፍቅር ስፋቱ፣ ርዝመቱ፣ ከፍታውና ጥልቀቱ ምን ያህል እንደሆነ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር የመገንዘብ ሃይልን እንድታገኙ ነው፡፡›› ኤፌ 3፡17-18

1. ኤፌ 3፡1-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2ትን ስናነብ ጳውሎስ ራሱን ለአህዛብ የክርስቶስ እስረኛ እንደሆነ ይናገራል፡፡ የሐዋ ሥራ 22፡21-22ት ላይ ረብሻ የተጀመረበትና ጳውሎስ ችግር ውስጥ የገባው ለምን ነበረ?
2. በቁ1-6 ላይ በተደጋጋሚ ተነግሮ የምናገኘው አንድ ቃል ምንድነው? በዚህ ክፍል ስትመለከት ጳውሎስ የእግዚአብሄርን ምስጢር መረዳት የቻለው በምን መንገድ ነበረ?
3. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ‹‹ምስጢር›› በመባል የተነገረው ነገር ያዘላቸው ሶስት አበይት ነገሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህን ሶስት ነገሮች ስታይ በሶስቱም ሃሳቦች ውስጥ ያለ አንድ ቃል ምንድነው?
4. ቁ8-9 ላይ ለጳውሎስ የተሰጡት ሁለት ሃላፊነቶች ምን ምንድናቸው? አንተስ ከቸርነቱ የተነሳ የተቀበልከውን የማይመረመረውን የክርስቶስ ባለጠግነት ለሰዎች ምን ያህል ትናገራለህ?
5. ቁ12-13 ላይ ወደ እግዚአብሄር መቅረብ የሚቻልበትን አንድ ብቸኛ መንገድ ይጠቁመናል፡፡ በዚህ ክፍል የምናነበው ይህ ብቸኛ መንገድ ምንድነው? ወደ እግዚአብሄር ስንቀርብ ሊኖረን ስለሚገባው የአቀራረብ ሁኔታ ምን ታያለህ? በአንተ አመለካከት ወደ እግዚአብሄር መቅረብ መቻላችን በህይወታችን ሊያስከትል የሚችለው ለውጥ ምንድነው ትላለህ? አንተስ ወደ እግዚአብሄር በድፍረትና በልበ ሙሉነት መቅረብ እንድትችል በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነሃል ወይ?
6. በኤፌ 1፡15-23 ላይ ጳውሎስ ለነዚህ ሰዎች የጸለየበት ዋነኛ ሃሳብ በአንድ አረፍተ ነገር ምንድነው? በኤፌ 3፡14-21 ውስጥስ ያለው ጸሎት ምንን አስመልክቶ ነው?
7. በቁ12-21 ውስጥ ጳውሎስ ለሶስት ዋና ዋና ነገሮች ሲጸልይ እንመለከታለን፡፡ የመጀመሪያው ጸሎቱ በምን ላይ ያተኮረ ነው? የውስጥ ሰውነት መጠንከር ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ዓይነቱ ጥንካሬ ሊገኝ የሚችለው በምን መንገድ ነው?
8. ቁ18 ላይ ጳውሎስ የጸለየላቸው ጸሎት ስለ ምንድነው? የክርስቶስን የፍቅር ምንነት ብቻ ሳይሆን የእነርሱም ፍቅር እንደ ዛፍ ሥር እንዲሰዱ፤ እንደ ህንጻ ደግሞ ወደላይ እንዲያድጉ ወይም እንዲታነጹ ይጸልይላቸዋል፡፡ አንተስ ፍቅርህ ወደታች የዘለቀ፣ ወደላይ አድጎ ደግሞ ለሰዎች እንደሚታይ ሆኖ የሚያድግ ነው ወይ? በክርስቶስ ፍቅር ከመደነቅ አልፈን እኛ የእርሱ ተከታይ ነን የምንል ሁላችን ፍቅራችን በጥልቀትና በቁመት ዘወትር እየጨመረና እያደገ እንዲሄድ ያስፈልጋል፡፡

# ጥናት ስድስት ኤፌ 4፡1-16

የጥናት ዓላማ፡- ለሰውነታችን እድገትና ጤንነት መላው ብልቶቻችን እንደሚገባ መስራት እንዳለባቸው ሁሉ፤ የክርስቶስ አካልም እንደሚገባ እንድታድግ ካስፈለገ እያንዳንዱ አማኝ እንደ ብልት የሚገባውን ድርሻውን ማድረግ እንደሚገባው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ከእርሱም የተነሳ አካል ሁሉ በሚያገናኘው ጅማት እየተያያዘና እየተጋጠመ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል፡፡›› ኤፌ 4፡16

1. ኤፌ 4፡1-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ ጳውሎስ የሚናገረው ጥሪ በመጀመሪያ ደረጃ የመጣው ከማን ዘንድ ነው? ጥሪውስ የመጣው በምንና በማን አማካኝነት ነው? በዚህ ቁጥር ውስጥ የጳውሎስ ልመና ምንድነው?
2. በቁ1-3 ላይ አማኞች ስለሚጠበቁባቸው አራት ነገሮችን ተናገር፡፡ ‹‹በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ጠብቁ›› ሲል አንድነቱ የሚጠብቁት እንጂ አዲስ የሚመሰርቱት እንዳልሆነ ይታያል፡፡ በኤፌ 2፡14-17 መሰረት አንድነቱ የተጀመረው በማን ነው? አንተስ በቅዱሳን መካከል ጌታ የመሰረተውን አንድነት ለመጠበቅ ምን ያህል ጥረት ታደርጋለህ?
3. እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አምስት ነገሮች ሰላምን ከመጠበቅ አንጻር አስተዋጽዖ የሚኖራቸው በምን መንገድ ነው ትላለህ?
4. አማኞችን አንድ የሚያደርጓቸው በቁ4-6 ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ምን ምንድናቸው? አንድነት የሚለው ሃሳብ በእግዚአብሄር አመለካከት በቤተ ክርስትያን ህይወት ውስጥ እንደዚህ ያለ ትልቅ ሥፍራ ተሰጥቶት የምናየው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንድነት የሚለው ሃሳብ በአንተስ ህይወት ውስጥ ምን ያህል ሥፍራ አለው?
5. በቁ7-8 ውስጥ ለአማኞች ስለተሰጠ ነገር እናነባለን፡፡ ይህንን ስጦታ አስመልክቶ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተነገሩ ቢያንስ ሶስት እውነቶችን ተናገር፡፡ ከዚህ ክፍል አነጋገር በመነሳት የጸጋ ስጦታን አስመልክቶ ስለ እያንዳንዳችን በድፍረት መናገር የምንችለው ነገር እውነት ቢኖር ምንድነው ትላለህ?
6. ቁ11-13ትን ስናነብ በተለይ ቁ11 ክርስቶስ ለቤተ ክርስትያን እንደሰጠ የተነገሩት ስጦታዎች ምን ምንድናቸው? የሰጣቸው ላይ ከስጦታዎቹ ጋራ ‹‹አንዳንዶች›› የሚል ተቀጢላ አነጋገር እንዳለ እናነባለን፡፡ ይህ ቃል በተጨማሪነት መግባቱ የሚጠቁመን ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
7. እነዚህ የተዘረዘሩት ሰዎች ለቤተ ክርስትያን የተሰጡበት ዋነኛው ምክንያት ለምንድነው ይላል? እስከ መቼ ድረስ ነው ቤተ ክርስትያን ይህንን ሥራ የምታከናውነው?
8. ለቤተ ክርስትያን የተሰጡት ሰዎችና እያንዳንዱ አማኝ የሚጠበቅበትን ሲያደርግ፤ ሊገኝ ስለሚችለው ውጤት ከቁ14-15 ውስጥ የምታያቸውን ነገሮች በመዘርዘር ተናገር፡፡
9. ቁ16ትን ስናነብ አማኞችን ቤተ ክርስትያንን በምን ምሳሌ ነው የሚስላት? አካል እንደሚገባው እንዲያድግና እንዲታነጽ ካስፈለገ የእያንዳንዱ ብልት አስተዋጽዖ ምን መሆን እንዳለበት ነው ቁ16 የሚነግረን? አንተስ እንደ ክርስቶስ ብልት በቤተ ክርስትያን ውስጥ የሚገባህን ተሳትፎና ሥራ ታከናውናለህ ወይ? አካሉ እንዲያድግና እንዲታነጽ ካስፈለገ አንተም በተሰጠህ የጸጋ ስጦታ ቅዱሳንን በማገልገል መሳተፍ ጌታ የሚጠብቅብህ ሃላፊነት እንደሆነ አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሰባት ኤፌ 4፡17-32

የጥናት ዓላማ፡- ከአንደበታችን የምናወጣው ቃል ሌሎችን ለመጉዳት ወይም ለማነጽና ለመጥቀም ከመቻል አልፎ፤ ለቤዛ ቀን የታተምንበትን መንፈስ ቅዱስ ሊያሳዝን ወይም ሊያስደስት ስለሚችል የምንናገረውን ቃል መመዘን እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንደአስፈላጊነቱ ሌሎችን የሚያንጽና ሰሚዎችን የሚጠቅም ቃል እንጂ የማይረባ ቃል ከአፋችሁ አይውጣ፡፡ ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሄር መንፈስ አታሳዝኑ፡፡›› ኤፌ 4፡29-30

1. ኤፌ 4፡17-32 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ17-19 ውስጥ ስለ አህዛብ አኗኗር የምታያቸውን ነገሮች ተናገር፡፡ ጳውሎስ ከዚህ አንጻር አማኞችን አደራ የሚለው ነገር ምንድነው? አንተስ ይህንን የጳውሎስ ምክር በህይወትህ ምን ያህል ትኩረት ሰጥተኸዋል?
2. ቁ17 የአህዛብን አዕምሮ፣ ቁ18 የአህዛብን ልብ፣ ቁ19 ደግሞ የአህዛብን ህሊና ምንነት ያሳዩናል፡፡ ከነዚህ ነገሮች አንጻር ስንመለከት የክርስትያን አዕምሮው፣ ልቡና ህሊናው በምን መንገድ ልዩ ሊሆን እንደሚገባ አስረዳ፡፡ ሮሜ 12፡1-2፣ 1ኛ ቆሮ 2፡16፣ 1ጢሞ 1፡19 ማንበብ ይረዳል፡፡
3. ቁ20 ላይ የኤፌሶን ሰዎች እንደ አህዛብ ላለመኖር ምክንያት አድርጎ የሚያቀርበው ነገር ምንድነው? በአንተ አመለካከት ጳውሎስ ይህንን ሲላቸው ምን ለማለት ፈልጎ ነው ትላህ?
4. በቁ20-24 ላይ ስንት ዓይነት ሰዎችን ትመለከታለህ? እነዚህ ሰዎች ምንና ምን በመባል ነው የሚጠሩት? ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ አሮጌው ሰው እና አዲሱ ሰው ሲል እንዴት ነው የምትረዳው?
5. በቁ22 ላይ አሮጌው ሰውነታችን ምን እንደሆነ ነው የሚነግረን? ከዚህ ሁኔታ የተነሳ በአሮጌው ሰውነታችን ላይ እንድናደርግ የሚያዘን ነገር ምንድነው? ቁ22-24 ባለው ክፍል አነጋገር አሮጌውን ሰውነታችንን አውልቀን መጣላችን አስፈላጊ ሆኖ የተገኘባቸው ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው?
6. በቁ20-24 ያለው ክፍል በምን መንገድ ነው በቁ25-32 ላለው ክፍል መሰረትና ወሳኝ ነገር ይሆናል ብለህ የምታምነው?
7. በቁ25-28 ውስጥ ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች መመሪያ የሰጠባቸው ሶስቱ ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እርስ በእርሳችን ውሸትን መነጋገር ልክ እንዳልሆነ የተሰጠው ምክንያት ምንድነው? ይህን ምክንያት ሲሰጥ ጳውሎስ ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ፡፡
8. በቁ29-32 ውስጥ ስትመለከት የእግዚአብሄርን መንፈስ ልናሳዝን የምንችልባቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? መንፈስ ቅዱስ በእነዚህና በመሳሰሉት ሁሉ የሚያዝን ከሆነ፤ በህይወትህ እርሱን ላለማሳዘን ምን ያህል ትጠነቀቃለህ? ከአፋችን የሚወጣው ቃል ሌሎችን ለመጉዳት ወይም ለማነጽና ለመጥቀም ከመቻል አልፎ ለቤዛ ቀን የታተምንበትን መንፈስ ቅዱስም ሊያሳዝን ወይም ሊያስደስት ስለሚችል የምንናገረውን ቃል ልንጠነቀቅ ይገባናል፡፡

# ጥናት ስምንት ኤፌ 5፡1-20

የጥናት ዓላማ፡- በመልካም ጤንነትና ኪስ ሙሉ በሆነበት ጊዜያት ብቻ ሳይሆን፤ ጤንነት ጎድሎ፣ ኪስ ባዶ በሆነበትና ኑሮ በከበደባቸው ሰዓታት ሁሉ እግዚአብሄር ሊመሰገን የሚገባው አምላክ መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…በልባችሁ ለጌታ ተቀኙ፣ አዚሙም፡፡ በዚህም እግዚአብሄር አብን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለሁሉ ነገር ሁልጊዜ አመስግኑ፡፡›› ኤፌ 5፡20

1. ኤፌ 5፡1-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 አነጋገር በፍቅር መመላለስ ማለት ምን ማለት ሆኖ ታየዋለህ? በዚህ ክፍል የምናየውንና እንድንለማመደው የታዘዝነውን የፍቅር አይነት በተግባር ሲፈጸም ታያለህ ወይ? ለምን ይመስልሃል ይህ የማይሆነው?
2. የእግዚአብሄር ህዝብ በቁ3 ላይ የተሰጠው መጠሪያ ምን የሚል ነው? በዚህ ቁጥር ላይ ለእግዚአብሄር ህዝብ የማይገቡ እንደሆኑ የተነገሩት ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በአንተ አመለካከት ከነዚህ ውስጥ ለብዙዎቻችን  እንደ አጸያፊ ነገር ሆኖ የማይታየንና አብረው ከተጠቀሱት ከሁለቱ ጋራ እኩል የማናየው የትኛውን ነው ብህ ታምናለህ? የራስህን ህይወት ስታየው ከስስት ምን ያህል የራቀ ነው?
3. ቁ4-5ት ላይ አነጋገርን አስመልክቶ ለክርስትያን እንደማይገቡ አድርጎ ጳውሎስ የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? በሌላ በኩል ደግሞ ከአንደበታቸው እንዲወጣ የሚያበረታታው ነገርስ ምንድነው? በቁ5 ላይ ስንመለከት በቁ3 ስለጠቀሳቸው ሶስት ሃጥያቶች በድጋሚ ይናገራል፡፡ በዚህ ቁጥር ውስጥ ስስታም (greed) ለተባለው የተሰጠው ሌላ ስም የሚል ነው? ለምን ይመስልሃል ይህ አይነት ከባድ ስም የተሰጠው?
4. ቁ8-9 የሚያነጻጽርልን ሁለቱ ዘመኖቻችን ምንና ምንድናቸው? በእነዚህ በሁለቱ መሃል ያለው ልዩነት ሰፊ ወይም ትልቅ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? የልዩነታቸውን ስፋት ይህ ክፍል ምን በማለት ነው የሚገልፅልን? በብርሃን የመመላለስ ወይም የመኖር ፍሬ ሆነው በዚህ ክፍል የተነገሩት ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
5. ቁ9-12 በማንበብ በተለይ ቁ9 ብርሃን መልካም ፍሬዎች እንዳሉት ተመልክተናል፡፡ በተቃራኒው ጨለማን ከፍሬ አንጻር ጳውሎስ እንዴት ነው የሚመለከተው? ፍሬ የሌለው ማለት በዚህ ክፍል አነጋገር ምንም ፍሬ አያፈራም ማለት ነው ወይ? አስረዳ፡፡
6. እንደ ብርሃን ልጆች መመላለስ የሚለው ሃሳብና፤ ጌታን ደስ የሚያሰኘውን መፈለግ ወይም ማወቅ የሚለው አነጋገር ያላቸው ግንኙነት ምንድነው ትላለህ? ቁ12 ላይ ‹‹ይልቁን ግለጡት›› ይላል፡፡ እንዴት ነው አማኞች የጨለማን ስራ ሊገልጡ የሚችሉት?
7. በቁ15 ላይ ጳውሎስ የኤፌሶንን ሰዎች የሚያስጠነቅቀው ስለምንድነው? ቁ15-18 ትን ስናነብ በጥበበኛ አማኝ አኗኗርና በሞኝ አማኝ አኗኗር መካከል ሊታዩ የሚችሉትን ቢያንስ ሶስት ነገሮች በማነጻጸር ተናገር፡፡
8. ቁ19-20 እግዚአብሄርን ስለምንና፣ መቼ እንድናመሰግነው ነው የሚነግረን? ጳውሎስ በቁ20 ላይና በ1ኛ ተሰ 5፡18 ላይ ስለሁሉ ነገር እግዚአብሄርን እንድናመሰግነው ሲነግረን ምን ለማለት የፈለገ ይመስልሃል? አንተስ እግዚአብሄርን የማመስገን ልምድህ ምን ይመስላል? ህይወት ተስተካክሎ፣ በመልካም ጤንነትና ኪስ ሙሉ በሆነበት ጊዜያት ብቻ ሳይሆን፤ ጤንነት በጎደለበት፣ ኪስ ባዶ በሆነበትና ኑሮ በከበደባቸው ሰዓታት ሁሉ እግዚአብሄር ሊመሰገን ይገባዋል፡፡

# ጥናት ዘጠኝ ኤፌ 5፡21-6፡9

የጥናት ዓላማ፡- ማናቸውም ዓይነት ግንኙነት ሊሳካና ሊያምር የሚችለው፤ ኢየሱስ በግንኙነቱ መሃል እንደ ሶስተኛ ሰው እንዳለ በመገንዘብብ እርሱን ለማስከበር የሚደረግ ጥረት ሲኖር ግንኙነቱ እንደሚሰምር ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ለክርስቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሃት የተነሳ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ፡፡›› ኤፌ 5፡21

1. ኤፌ 5፡21-6፡9 በአንድነት ይነበብ፡፡ ዛሬ ባነበብነው ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ያስተማረባቸው ስንት ዓይነት ግንኙነቶችን ትመለከታለህ? እነዚህ ግንኙነቶች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር፡፡
2. ቁ21-24 ላይ ስናነብ ለሁለቱም በጋራ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ምን የሚል ነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለሚስቲቱ በግል የተሰጧት ምን ትዕዛዞች ታያለህ? የሚስትን ለባል መገዛት ጉዳይ ጳውሎስ ከምን ጋራ በማነጻጸር ነው ያቀረበው? ለባሎች የተሰጠውን ትዕዛዝ በአንድ አረፍተ ነገር ተናገር፡፡
3. በቁ21-33 ውስጥ ‹‹ክርስቶስ›› እና ‹‹ቤተ ክርስትያን›› የሚሉትን ሃሳቦች በአንድነት ስንት ቦታ እናገኛቸዋለን? ባልና ሚስትን አተኩሮ በሚናገር ክፍል ውስጥ ክርስቶስና ቤተ ክርስትያንን ልክ እንደዋነኛ ተዋናኝ ሆነው የቀረቡበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ?
4. በኤፌ 5፡31-33 ላይ ጳውሎስ ‹‹ይህ ጥልቅ ምስጢር ነው›› እያለ የሚናገርለት ነገር ምንድነው? በባልና በሚስት መሃል አንዳቸው ለሌላቸው ያለባቸውን ሃላፊነት ጳውሎስ የጠቀለለው ምን በማለት ነው?
5. በኤፌ 6፡1-4 ስናነብ ልጆች በቤተሰብ ግንኙነት ውስጥ ምን እንዲያደርጉ ነው የሚጠየቁት? አባቶችስ በዚህ ግንኙነት ምን ይጠበቅባቸዋል? ‹‹በጌታ ታዘዙ›› እና ‹‹በጌታ ምክርና ተግሳጽ›› የሚሉት አነጋገሮች ስለዚህ ግንኙነት ምን ይጠቁመናል?
6. ቁ5-9 ባሪያና ጌታ ወይም የአሁኑ ዘመን ሰራተኛና አሰሪ ለእያንዳንዳቸው የተሰጣቸው ምክር ምን እንደሆነ አጠር አድርገህ በራስህ ቋንቋ ተናገር፡፡ በዚህ ግንኙነት ውስጥስ ጌታ ክርስቶስ ምን ያህል ሥፍራ ተሰጥቶት ታያለህ? በዚህ ግን
7. ለባልና ሚስት፣ ለወላጆችና ለልጆች እና ለባሪያና ጌታ ወይም አሰሪና ሰሪ የተሰጡት መመሪያዎች የለክርስቶስን ጌትነት ያልተቀበሉትን ወይም ያላመኑትን ሰዎች እንዲኖሩበት መጠበቅ ስህተት የሚሆነው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ?
8. እንደ ቁ21 አነጋገር ጳውሎስ በግንኙነት መሃል ማዕከላዊውን ሥፍራ ሰጥቶት የምንመለከተው ለማን ነው? ይህንን ለማለት እንዴት ቻልክ? በትዳር፣ በቤት፣ ወይም በስራ ባለህ ግንኙነት ክርስቶስ ምን ያህል ቦታ ተሰጥቶታል? ግንኙነቶችህ ሊሰምሩና ስኬታማ ሊሆኑ የሚችሉት፤ ኢየሱስ የግንኙነቱ መሰረት ተደርጎ ሲታይና ፈቃዱን ለመፈጸም ልብህን ስታዘጋጅ ብቻ ነው፡፡

# ጥናት አሥር ኤፌ. 6፡10-24

የጥናት ዓላማ፡- አማኝ እያንዳንዱን ቀን፣ ሰዓትና፣ ደቂቃ ሁሉ በጦርነት ላይ መሆኑን ሳይዘነጋ በንቃት የሚመላለስ ብቻ ሳይሆን፤ ለሌሎችም ቅዱሳኑንና አገልጋዮች ሁሉ በጸሎት እየተጋደለ የሚያግዝ መከታ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በጸሎትና በልመና ሁሉ፤ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤ ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ፡፡›› ኤፌ. 6፡18

1. ኤፌ. 6፡10-24 በአንድነት ይነበብ፡፡ ክርስትያን የእግዚአብሄርን ሙሉ የጦር ዕቃ መልበስ የሚያስፈልገው ምክንያት ለምንድነው? የጦር ዕቃው ‹‹የእግዚአብሄር›› ተብሎ የተጠራበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ?
2. በቁ10-13 ባለው ክፍል ውስጥ ጳውሎስ የክርስትና ህይወት ምን መሆኑን ነው ሊያስረዳን የሚሞክረው? ስለጦርነቱ ዓይነት የሚነግረን ምንድነው? ስለጠላታችንስ ማንነት ምን ይነግረናል? ጳውሎስ ጠላት የሚለውና አንተ ስትዋጋ ዘመንህን የምትጨርሰው እርሱ ጠላት ከሚለው ወይስ ከሰዎች ጋራ ነው?
3. የእግዚአብሄር ሙሉ የጦር ዕቃ ተብለው በቁ14-18 ላይ የተዘረዘሩት ስድስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? የመንፈስ ሰይፍ ወይም የእግዚአብሄር ቃል በመባል የተጠራው ዕቃ ጦር ከሌሎቹ የሚለይበት አንድ ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? ይህንን የጦር ዕቃ ኢየሱስ በምድር ህይወቱ ከተጠቀመበት ጊዜ የምታስታውሰውን አንዱን ጊዜ ተናገር፡፡ ይህንን የጦር ዕቃ ለመጠቀም የሚጠይቀው ነገር አንድ ነገር ምንድነው?
4. የእግዚአብሄር የጦር ዕቃ በመባል ከተዘረዘሩት መሃል ጀርባችንን ለመከላከል የተሰጠን መሳሪያ ትመለከታለህ ወይ? ለጀርባችን መከላከያ ያልተሰጠን ምክንያት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
5. በቁ18 ላይ ‹‹ይህንም በማሰብ›› ሲል የሚናገረው ስለየትኛው ነገር ይመስልሃል? ከዚህስ የተነሳ አንባቢዎቹ እንዲያደርጉት ያዘዛቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
6. ቁ19-20 ጳውሎስ በዚህ ክፍል ቅዱሳን እንዲጸልዩለት የሚጠይቃቸው በምን ርዕሶች ላይ እንዲጸልዩለት ነው? ‹‹ቃል ይሰጠኝ ዘንድ›› ‹‹መናገር የሚገባኝን›› የሚሉት አነጋገሮች ወንጌልን እናገለግላለን ለሚሉ ሰዎች ምን ሊያስተምራቸው ይችላል ብለህ ታናለህ?
7. በቁ21-24 እና ቆላ 4፡7-9 ላይ ለጳውሎስ በመልዕክተኛነት የሚያገለግለው ሰው ማንነው? ስለዚህ ሰው በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የተነገሩትን ነገሮች ዘርዝር፡፡ ደብዳቤ አመላላሽነቱን በታማኝነት እንደሚሰራው አንተስ ከጌታ የተቀበልከው አንሶብህና የተናቀ አድርገህ ታየዋለህ ወይስ በታማኝነት ታከናውነዋህ?
8. በተለይም የዛሬውን ጥናታችን በመመርኮዝና ቁ18ትን ስናይ፤ ቅዱሳንን በጸሎት መርዳት እጅግ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝበት ዋነኛ ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ በዚህ በጦርነት ህይወት ውስጥ ሌሎች ቅዱሳን በጸሎትህ ውስጥ አሉ ወይ? እያንዳንዱ ክርስትያን በውግያ መሃል ለራሱ ከመዋጋት አልፎ ሌሎቹንም ቅዱሳን በጸሎት በመደገፍ እርስ በእርስ አንዱ ለአንዱ ደጀን መቆም አስፈላጊ ነገር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡